# ሰዎች የክርስቶስን የደኅንነት ትምህርት ለመቀበል ለምን ይቸገራሉ?

ስለአንድ እየሰከሩ ስላስቸገሩ ቄስ የሚነገር ታሪክ ነበር። እኝህ ቄስ ኅብረተሰቡን ለማስተማር በሚሞክሩበት ጊዜ በመጠጥ ጸባያቸው ምክንያት፡- 'አይ! እርስዎን ብሎ አስተማሪ ደግሞ! ኧረ ወዲያ!' እያለ ምእመኑ አልሰማ ሲላቸው፤ አንድ ቀን፡- 'እኔ የምለው፤ ለመሆኑ ቁስል ባለባት አህያ እህል በጆንያ ተጭኖ ቢመጣላችሁ፣ ከእህሉ አትበሉም ማለት ነው?' ብለው ጠየቁ ይባላል።

ዛሬ የክርስቶስ የምሥራች መልዕክት/'ወንጌል' ሲሰበክ ወደ አዳማጭ ልብ፥ ወደ የውስጥ ማንነት የማይደርስበት ምክንያቶች ምንድናቸው?

በአንድ በኩል ‘ጴንጤዎች’ ወይም የፕሮቴስታንት የክርስትና ዘርፍ አማኞች ሌሎችን ስለ ክርስቶስ እንመሥክር ብለው ሲቀርቡ በአብዛኛው የተከፈተ ልብ እንደማይገጥማቸው ይመሰክራሉ። አንዳንዶች ‘ይህ የሰይጣን ሥራ ነው’ ብለው ይደመድማሉ። አንዳንዶች ደግሞ ‘ጴንጤ’ የሚለው ስያሜ በራሱ እንደ አጥር ሆኖ እንደሚያሰናክል ያምናሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ማንነቱ ከመልእክቱ ጋር እየተጋጨ** ያስቸገረው ሐዋርያው ጳውሎስ ነበር። አንደኛ የክርስትና አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ክርስቲያኖችን እያሳደደ፤ እያሳሰረ እና እያስገደለ ስለነበር አድማጮችና እንደዚሁም የክርስቶስ አገልጋዮች የነበሩ ሊያምኑት ተቸግረው ነበር። ሁለተኛ የሚያስተላልፈው መልእክት አይሁዶችን የሚፈታተን ስለነበር ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞታል።

ሲጀመር አንስቶ የክርስቶስን የምሥራች መልእክት ሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ፣ በሙሉ ደስታ እና እምነት አልተቀበሉትም። እንኳንም ሰው ሰብኮ ይቅርና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ ሰብኮ ብዙዎች እንዳልተቀበሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመማር እንችላለን። ለምሳሌ ማርቆስ በጻፈው ወንጌል በምዕራፍ 6 ላይ እንደምናነበው ክርስቶስ በገዛ እራሱ አገር፣ ባደገባት በናዝሬት ከተማ ‘ይህ ጸራቢው የማርያም ልጅ አይደለም እንዴ?’ **ብለው እንደናቁት ወይም መልእክቱን እና ማንነቱን ለመቀበል እንደተሰናከሉ ለማየት እንችላለን**። እንደዚሁም በሌላ በተዘገቡልን መማሪያ ምንባቦች አይሁዶች ወይም ፈሪሳውያን፣ ‘እኛ እንደ አባት አብራሃም አለን አንተ ማነህ?’ ብለው **እንደተመጻደቁበትም** እንመለከታለን (ዮሐ 8፡-39)። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል በንቀት የማንቀበልበት ጊዜ አለ ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ **ከተለማመድነውና ከለመድነው ሥርዓትና ባህል ውጪ የሆነን መልእክት በግብዝነት ለመቀበል የምንቸገርበት** ጊዜ ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ፤ ጻፎችና ፈሪሳውያን ክርስቶስ እነርሱ ከተለማመዱት ሥርዓት ወይም ባህል ውጪ፣ አለዚያም ሕግ ነው ብለው ከያዙት አሰራር ውጪ ሲያስተምር ወይም ሲገብር ሲያዩት/ሲያገኙት በመቆጣት፣ በመጠየፍ ‘እንዴት እንደዚህ ታደርጋለህ?’ እንደገናም ‘ለምን ደቀ መዛሙርቶችህ እንደዚህና እንደዚህ ያደርጋሉ’ በማለት መሠረቱን፣ ዋነኛውን መልእክት ሳይገነዘቡ እንደቀሩም እናያለን። ለዚህ ምሳሌ ለማቅረብ ቢያስፈልግ - የሰንበትን ክብር በሚመለከት፣ እለእጅ መታጠብ ሥርዓት፣ እንደዚሁም ስለ ጾም ጉዳይ የተነሳው ግጭት በቂ ይሆናሉ።

ከክርስቶስ ጋር ለሦስት ዓመት ገደማ አብረው ሲዘዋወሩ የነበሩትም ደቀ መዛሙርት፤ ምንም እንኳን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያመኑ እና በዓይናቸው በርካታ ተአምራትን ለመፈጸሙ ምስክሮች የነበሩ ቢሆንም፤ በተደጋጋሚ እርሱንና ማንነቱን ሙሉ ለሙሉ ባለመረዳታቸው፣ ያስተማረውን እና **የነገራቸውን ትምህርቶችና እውነቶች በሙላት ስላልተረዱትና ስላልገባቸው እንደዚሁም የራሳቸው ወይም የስጋቸው ፍላጎት**

**ስላየለባቸው** ከአንዱም ሁለት ሦስቴ የትምህርቱን አንኳር ሃሳብ ሳይረዱ ወይም ሳይቀበሉ የቀሩበት በርካታ ምሳሌዎች በአራቱም ወንጌላት ለትምህርታችን ተዘግበው ይገኛሉ።

ዘልቀን ስናይ ደግሞ የመጀመሪያው የክርስቲያን ሰማዕት ዲያቆን እስጢፋኖስ በድንጋይ የተወገረበት ምክንያት ወንጌልን ስለሰበከ ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስ እና ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ወንጌል በሰበኩ ጊዜ እንደዚሁ መከራ፣ እሥራት፣ ንቀት፣ ስድብ፣ ስደት ብሎም ሞት ገጥሟቸዋል። አይሁዶች የሚጠብቁት መሲሕ ከንጉሣዊ ቤተሰብ የሆነ እንጂ ከድሃ ቤተሰብ ተወልዶ ሊሞት የሚመጣ አዳኝ ነው ብለው በፍጹም አልጠበቁም ነበር። በተለይም የእርግማን ሞት (በመስቀል ላይ የሚሞት እርጉም ነበርና)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በላከው ደብዳቤ እንደገለጸው ነው፦ 'እኛ ግን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው' (1ቆሮ 1፡-23)። መስቀል እና በመስቀል ሞት የዘላለም ሕይወትና ደኅንነት ይገኛል የሚለው **የክርስትና የምሥራች ቃል ወይ መሰናከያ ወይ ሞኝነት ሆኖ ሰዎች ለመቀበል ይቋረዳሉ ማለት ነው**።

እንደ ኒቆዲሞስ **በፍርሃት ወይም በሐፍረት** የተዋጠ ደግሞ ይኖር ይሆናል። እንደዚህ ዓይነቱ ከሌሎች ላለመለየት/'ከሰፊው ሕዝብ' ጋር አብሮ ለመሆን አለዚያም ከሰዎች ፍርድ፣ ዓይን፣ ትችት፣ መታዘብ ለመሸሽ ሲል በድብቅ የክርስቶስን ማንነት፣ ትምህርት ለመከታተል የሚገዳደር አይጠፋም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት እንደምንችለው፤ አንዳንድ ጊዜ **የብሔራዊነት ስሜት ወይም የፖለቲካ አቋም ከክርስቶስ ዋነኛ እና መሠረታዊ መልእክት ሊጋርደን እንደሚችል መመልከት ይቻላል**። የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎችና አስተማሪዎች እንደሚያስረዱን ክርስቶስ ኢየሱስን ሲከተል ቆይቶ በስተመጨረሻ ላይ ለመካድ የበቃው ደቀ መዝሙሩ ይሁዳ ከግል አጀንዳው በተጨማሪ የፖለቲካም አጀንዳ እንደነበረው ይጠቁማሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ፤ ትንሳኤውን ሳይሰሙ፤ ወደ ኤማሆስ በትካዜ ተውጠው ሲጓዙ ክርስቶስ ተገልጦላቸው አብሮ ሲጓዝ ያነሱት ነጥብ 'እኛስ የእስራኤልን መንግሥት ይመልስልናል ብለን አስበን ነበር' የሚል ነበር። እንግዲህ ክርስቶስ በጉዞአቸው ባይገናኛቸው ኖሮ በፖለቲካ አቋማቸው ሕላዊ ከሆነው ከክርስቶስ ወንጌል ሳይገናኙ በእርሱ መንግሥት ሳይካተቱ ይቀሩ ነበር።

ሌላ ምሳሌ፤ የክርስቶስን መልእክት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ሳይሆን **በሥጋ ወይም intellectually ለመረዳት መሞከር ነው**። ክርስቶስ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ እንደምናገኘው 'እኔ ከሰማይ የወረድኩኝ እንጀራ ነኝ' ብሎ ስላላቸው፤ ቃሉ ስለከበዳቸው ብዙ ደቀመዛሙርት ክርስቶስን ከመከተል እንደሸሹ ለመመልከት እንችላለን።

በመጨረሻ ላነሳው የምፈልገው ነጥብ **ለእግዚአብሔር መልእክት የሚገባውን ትኩረት አለመስጠት የሚለውን**። በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ማንነት፣ ማወቅ መረዳትና መቀበል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባውን ዕለታዊ ግንኙነት፣ እንደዚሁም እርሱ ከኛ የሚጠብቅብንን እውነተኛ አምልኮ እና አገልግሎት ችላ በማለት የእግዚአብሔር መልዕክት፣ ምሪት፣ ማስጠንቀቂያ፣ በረከት ወዘተ… ሳያገኘን እንቀራለን። የዚህ እውነታ መጨረሻው በጣም አሳሳቢ እና አስከፊ መሆኑን አጥብቆ ለመገንዘብ እንዲያመቸን የኖኅን ምሳሌ ማቅረብ እንችላለን። ኖኅ የንስሐን እና የውሃ ጥፋትን መልእክት ለሕዝቡ 120 ዓመት ሙሉ ሲሰብክ ነበር። ሰምተው የተረፉት ሰዎች ግን **8** ብቻ ናቸው!!